የትራንስፖርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT

**መመሪያ ቁጥር 1/2012**

**የኮቪድ 19 ስርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ መመሪያ (ዋና ዋና ሀሳቦች)**

✓ **የአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት በተመለከተ**

- ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎቶች ሲሰጡ የሚያስከፍሉትን የታሪፍ ጭማሪ በተመለከተ ከመደበኛ ዋጋው 50 ከመቶ ጭማሪ የሚኖረው ሆኖ ዝርዝሩ በባለስልጣኑ እንደሚወሰን፤

- የአገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በየመናሃሪያዎቹ በተመሳሳይ ሰዓት ደርሰው ለሰዎች ንክኪ እና መጠጋጋት ዕድል እንዳይፈጥሩ የአጭር ርቀት እና የረጅም ርቀት የህዝብ ማመላለሻዎች የመነሀሪያ መግቢያ እና መውጫ ሰዓት እንዲለያይ ይደረጋል፤ በቀን ካሉት 232 መስመሮች በአማካይ 82 ብቻ እንዲወጡ ይደረጋሉ፤

- ማንኛውም ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚችለው ከንጋቱ 12:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ መሆኑን፤

- በየመናኻሪያዎቹ ላይ አገልግሎት የሚያገኙ ተሳፋሪዎች የጤና ሚኒስቴርና የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ወይም በክልሎች የሚገኙ ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በሚያዘጋጁት ቅጽ መሰረት የመመዝገብ ግዴታ እንዲኖርባቸው የማድረግ ስራዎች ይኖራሉ ይህም ማለት ችግር ቢፈጠር የነበሩትን ተሳፋሪዎች በቀላሉ ለማግኘት እንዲቻል፤

✓ **የጭነት ተሽከርካሪዎች**

- የጭነት ተሽከርካሪዎች መጫን የሚፈቀድላቸው ከአሽከርካሪው በተጨማሪ አንድ ሠው ብቻ ነው።

✓ **የግል እና የመንግስት ተሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ**

- የግልም ይሁን የመንግስት ተሽከርካሪዎች መጫን የሚችሉትከሽከካሪው ዉጪ የወንበር መጫን አቅማቸው 50 በመቶ ብቻ ይሆናል፤

- የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የሚቻለው የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ሙሉ ቁጥር ወይም ጎደሎ ቁጥር በሚል እየተለዩ አገልግሎት እንደሚሰጡ፤ የሠሌዳ ቁጥራቸው የመጨረሻው ቁጥር ሙሉ ቁጥር የሆነ የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎች ብቻ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን መንቀሳቀስ የሚችል ሲሆን በዚህ ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ጎደል ቁጥር የሆነ የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ አይፈቀድላቸውም። የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ዜሮ የሆነ የግል መኪኖች እንደ ሙሉ ቁጥር ይወሰዳሉ፤ እንዲሁም በሚቀጥለው ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ጎደሎ የሆነ የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ የሚፈቀድላቸው ሲሆን በዚህ ቀን የሠሌዳቸው የመጨረሻ ቁጥር ሙለ ቁጥር የሆነ የግል ወይም የቤት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ አይፈቀድላቸውም፤

- በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ከስራቸው ጸባይ አንጻር በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፤ በደንቡ ወይም በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ውስጥ የተገለጹት ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ ሰዎች ከባለስልጣኑ (ከፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን) በሚሰጣቸው ልዩ የይለፍ ፈቃድ ብቻ እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል።

✓ **የሰራተኞች የስራ ሰዓትን በሚመለከት**

- የፌደራል ሠራተኞች ሥራ መግቢያ ሰዓት ከጠዋቱ 1:30 ሲሆን ከስራ መውጫ ሰዓት ደግሞ ከቀኑ 9:30 እንደሚሆን፤ የሥራ ሰዓት ሽግሽጉም ሠራተኞቹ በስራ ሰዓት መካከል የሚያገኙትን የእረፍት ጊዜ አያስቀርባቸውም፤

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኞች የስራ መግቢያ ሰዓት ከጠዋቱ 3:30 ሲሆን ከስራ መውጫ ሰዓት ደግሞ ከቀኑ 11:30 ይሆናል። ይህ የሰዓት ሽግሽግ ሠራተኞቹ በስራ ሰዓት በመሃል የሚያገኙትን የእረፍት ጊዜ አያስቀርባቸውም።

- ሌሎች የክልል መስተዳደሮች የስራ ሰዓትን በሚመለከት የዚህን መመሪያ ዓላማ ሳይቃረን ክልሎች ከየራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አሰራር እንዲዘረጉ እንደሚደረግ፤

- የግል አሰሪዎች የሥራ መግቢያ እና መውጫ ሰዓት እስከአሁን ድረስ የሚጠቀሙበት መደበኛው የሥራ ሰዓታቸው እንዳለ እንደሚቀጥል፤

✓ **የከተማ ትራንስፖርትን በተመለከተ**

- የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር መንገደኞችን መጓጓዝ የሚችለው ከዚህ በፊት ሲጭን በነበረው 25 በመቶ ብቻ ይሆናል

- የከተማ ውስጥ አውቶብሶች መጫን የተፈቀደላቸው በመደበኛነት ሲጭኑ ከነበረው መጠን 50% ብቻ ነው፤

- የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶች መጫን የሚችሉት የወንበራቸውን 50% ብቻ ነው፤

- የከተማ ውስጥ ታክሲዎች /በየትኛውም የሠሌዳ መለያ ኮድ የሚሰሩ/ መጫን የሚችሉት በህግ ከተፈቀደላቸው የሠው ብዛት 50% ብቻ ነው፤

- ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች መጫን የሚችሉት ከአሽከርካሪው በተጨማሪ አንድ ሠው ብቻ ነው፤

- ባለ ሁለት እግር የሞተር ወይም ሞተር አልባ ሳይክሎች ከአሽከርካሪው ሌላ ምንም ሰው መጫን አይፈቀድላቸውም፤

- ለሰው ማመላሻ አገልግሎት የሚሰጡት በእንስሳት የሚጎፉ ጋሪዎች መጫን የሚችሉት ከባለጋሪው በተጨማሪ አንድ ሰው ብቻ ነው።

**ቅጣትን በተመለከተ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ዝርዝር አፈጻጸም ያዘጋጃል።**